


# ከሥጋዊ ክርስትና
# እንዴት ነጻ መሆን ይቻላል?

**5-2**

## ሀ. በመስቀሉ ኃይል

የመስቀሉን ኃይል ጳውሎስ በሮሜ 8፥3-4 ላይ ገልጾታል። እግዚአብሔር በእኛ ኃጢአተኛ ሥጋ ምትክ ክርስቶስን በመስቀል ላይ ቸንክሮታል። በዚያም የእኛን ኃጢአተኛ ህይወት ቀደሰው። ከሥጋዊ የክርስትና ህይወት ለማምለጥ ከሚረዱት ቁልፎች መካከል አንደኛው የክርስቶስ መስቀል ነው። በኃጢአት የበለዘውን ህይወታችንን ለማዳን በእኛ ምትክ ኢየሱስ ሞተ። በመስቀል የሞተውን ኢየሱስን ስናይ የእኛን ኃጢአት የሞላበትን ሥጋዊ ህይወት ለብሶ እናየዋለን። በእኛ ምትክ የሞተውን ሰው እንወደዋለን፤ ከእርሱም ጋር ለዘለዓለም እንጣበልቃለን እንጂ ከእርሱ የሚያሸሽንን ኃጢአት ለመሥራት አንፈልግም። በሞቱ እኛና ኢየሱስ አንድ እንሆናለን። ማለትም ለራሳችን መኖር በዚያ መስቀል ላይ ያበቃ ይሆናል። ከዚህ በፊት በክርስትና ህይወታችን አሸናፊ ሕይወት ለመኖር ያቃተን፥ ኃዘንና ብቸኝነት፣ ብዙ መሸነፍም ሊደርስብን የቻለው በሞቱ ከክርስቶስ ጋር ያልተባበርን በመሆኑ ብቻ ነው። “በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ” ይላል ሉቃስ 9፥23። እንግዲህ ሥጋችን በመንፈሳዊ ጉዟችን ላይ እንቅፋት ለመሆን ሲታገለን፥ ከክርስቶስ ጋር መሞታችንን ለሥጋችን እንንገረው። በእኛና በሥጋችን መካከል የክርስቶስ መስቀል ቆሟል። ክርስቶስ በተነሳበት በአዲስ ህይወት እንጂ እንደገና ለሞተ ለበሰበሰና ለገማ አሮጌ ሕይወት እንደገና አንኖርም በማለት ለጠላታችን እናስታውቀው።

## ለ. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል

ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ራሱን ለአብ ያለነቀፋ ማቅረብ እንደቻለው ሁሉ እኛም ከደካማ ሥጋዊ መንፈስ ነጻ ለመሆን የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ከዚህ ከሚሞት ደካማ ሥጋ ለማምለጥ የምንችለው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በህይወታችን ያለ እንደሆነ ነው። ያም የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ታይቶ የሚጠፋ ሳይሆን የማያቋርጥ የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው።

## ሐ. ፈቃድን በማስገዛት

በብዙ ክርስቲያኖች ሕይወት አይሎ የሚታየው ራስን የማስቀደም መንፈስ መወገድ ይገባዋል። የደካማ ሥጋ ፍሬ ውጤት የሆነውን ራስን አተልቆ ማሳየትን ማንኛውም ክርስትያን ከሕይወቱ አስወጥቶ ከክርስቶስ መስቀል ላይ መስቀል ያስፈልገዋል። ክርስቶስ መለኮታዊነቱን ትቶ ከወረደ እኛ ደግሞ ኃጢአተኛውን ሥጋችንን መካድ አለብን። ክርስቶስ መለኮታዊ ኃይሉን እንዲጠቀም ፈተና እንደቀረበለት እኛ ደግሞ በአሮጌው ህይወት ውስጥ እንድንመላለስ ፈተና ይቀርብልናል። ድል ማግኘት የምንችለው ያንን አሮጌ ተፈጥሮ በክርስቶስ መስቀል ሥር ያኖርነው እንደሆነ ነው።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**